Evangelical Mekane Yesus Lutheran Fellowship in North America
1566 Thomas Ave W. St. Paul, MN
651-621-9866
syderessa@gmail.com

A Statement on Human Sexuality: Evangelical Mekane Yesus Lutheran Fellowship in North America.

በሰሜን አሜሪካ የወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ሉተራን ሕብረት፣ ስለ ሰዎች የጾታና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሥነ-ምግባር የወጣ መግለጫ

ይህ የኢትዮጲያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በስነ-ጾታ፣ በጋብቻና በግብረ ሰዶማዊነት ጉዳዮች ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሉተራዊ አስተምህሮዋን እንድትጠብቅ ከወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ሉተራን ሕብረት በሰሜን አሜርካ የቀረበ ጥሪና የአቋም መግለጫ ነው።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የሰዎች የጾታና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን በሚመለከት መመሪያዋ የእግዚአብሔር ቃል እና በቀደምት ሉተራውያን አስተምህሮ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ግልጽ ነው።ንጹህን ወንጌል ለኢትዮጵያና ለሌሎች ዓለማትም ለማድረስ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸውና የረጅም ጊዜ የወንጌል አጋሮቿዋ የሆኑት የአሜርካ ወንጌላዊት ሉተራዊት ቤተ ክርስቲያን (ELCA) እና የስዊድን ቤተ ክርስቲያን (Church of Sweden) የሰዎች የጾታና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን በሚመለከት ከእግዚአብሔር ቃልና የቀደሙት አባቶቻቸዉ ካሰተማሩት ንጹህ አስተምሮ አፈንግጠው የተመሳሳይ ጾታ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ሲቀበሉ ቤተ ክርስቲያናችን በማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል እና በሉተራን አስተምሮ ጽኑ መሠረት ላይ ቆማ ከድርጊታቸዉ እንዲመለሱ በተደጋጋሚ ደብዳቤ በመጻፍ ሐዋሪያዊና ሚሲዮናዊ ሃላፊነትዋን ተወጥታለች። እየተወጣችም ትገኛለች። ሆኖም ግን እነዚህ ሁለት ወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ከድርጊታቸው ባለመመለስ ከእግዚአብሔር ቃልና ከተፈጥሮ ሥርዓት ያፈነገጠውን የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለመፈጸም እና በዚህ ልምምድ ዉስጥ ያሉ ቀሳዉስትን ለአገልግሎት ለመቀበል ዉሳኔ ሲያስተላልፉ ቤተ ክርስቲያናችን ባለማመንታት ግንኙነትዋን አቋርጣለች። ይህም ውሳኔዋ በዓለም ላይ በተበተኑና በአገር ውስጥ ባሉት ምእመናኖቿዋና ለእግዚአብሔር ቃል አክብሮት ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዘንድ የተወደሰ ውሳኔ ነው።

ከእነዚህ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የነበራትን ግንኙነት ማቋረጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ተከትሎና በጥልቅ የሥነ መለኮት ጥናት ተደግፎ የተወሰነ መሆኑ የታወቀ ነው። በይፋ ከሚጠቀሱትም መካከል እ.ኤ.አ. በ2012 የተካሄደዉ 19ኛዉ አቢይ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያኒቱ በግምቢ ከተማ ባካሄደቸው 6ተኛ ካውንስል የሰዎች ጾታና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን በሚመለከት ከቃሉ ስላፈነገጡት ሉተራዉያን አብያተ ክርስቲያናት በቀረበው ጥልቅ ጥናት ላይ ተመስርቶ፤ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እና ሌሎችም ተመሳሰይ ውሳኔ ከሚወስኑ ጋር የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ማንኛውንም ግንኙነት እንድታቋርጥ የተላለፈው የፖሊሲ ውሳኔዎች ዋናዎቹ ናቸው። ውሳኔዋም ቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረቷ ለሆነው የእግዚአብሔር ቃል እና ለቀደምት የሉተራን አስተምህሮ ያላትን የማያወላዳ አቋም ያረጋግጣል።

ሆኖም ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ከዚህ የፖሊሲ ውሳኔዋ ባፈነገጠ መልኩ እ.ኤ.አ. በ2023 ዓ.ም. በተሰበሰበው ካዉንስል ስብሰባ ላይ “የትድግና ተልእኮ” (rescue mission) በሚል ስያሜ በቀረበው አጀንዳ በፖሊሲ ውሳኔ ከተለየቻቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት ለመጀመር ስልታዊ ጥናት ይደረግ ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱን ሰምተን እጅግ ደንግጠናል፤ አጅግም አዝናናል። ይህም አካሄድ ያሳዘነን የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አካል በሆነው አብይ ጉባኤ የተወሰነውን የቤተ ክርስቲያኒቱን የፖሊሲ ውሳኔ መጻራሩ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነት፣ ጤናማ ሕብረት፣ ዕድገትና፣ የወንጌል ምስክርነት አገልግሎት አጅግ አስጊና አደገኛ ውሳኔ በመሆኑ ጭምር ነው።

ስለዚህም እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንኖር የቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናንና አገልጋዮች፤ ከጁላይ 17-21፣2024 በቺካጐ እልኖይስ በተደረገው 19ኛው ዓመታዊ ኮንፍራንሳችን፡ ይህንን የአቋም መግለጫ ለማውጣት ተገድደናል።

የአቋም መግለጫ

እኛ በሰሜን አሜሪካ የወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ሉተራን ሕብረት ስለ ሰዎች ጾታና ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሥነ ምግባር ያለን መረዳትና እምነት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ቃል ወይንም በቅዱሳት መጻሕፍትና በሉተራን አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንገልጻለን። ይህንንም መሠረታዊ እምነታችንን የሚገዳደረውን የዘመኑን ትምህርትና አመለካከቶች በተለይም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የተመሳሳይ ጾታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ካጸደቁትና ከሚያራምዱት ከአሜርካ ወንጌላዊት ሉተራዊያን ቤተ ክርስቲያን (ELCA) እና ከስዊድን ቤተ ክርስቲያን (Church of Sweden) ጋር “የትድግና ተልእኮ” (rescue mission) በሚል መርህ ግንኙነቷን ለማደስ የምታደርገውን እንቅስቃሴ በጥብቅ እንቃወማለን።

ምክንያቱም፡-

1. የተመሳሳይ ጾታ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ውሳኔአቸው ከእግዚአብሔር ቃልና ከሉተራን መሠረተ እምነት ጋር የሚጣረስ በመሆኑ፣
2. የቤተ ክርስቲያኒቱን 19ኛ አቢይ ጉባኤ ውሳኔ የጣሰ ስለሆነ፣
3. በቤተ ክርስቲያኒቷ አንድነትና በቀጣይ ትውልድ ላይ የሚያመጣውን ከባድ አደጋ ያላገናዘበ ስለሆነ ጭምር ነው።

ይህ የአቋም መግለጫ የሚወክለው በእግዚአብሔር የተደነገገውን ደግሞም በቅዱሳት መጻሕፍት እና በሉተራን አስተምሯችን የተነገረውን የጋብቻን እና የሰውን ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ቅድስና በመጠበቅ ረገድ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ከቤተ እምነቶች ጋር በምታደርጋቸው ግንኙነቶቿ ውስጥ የአስተምህሮ ታማኝነትን እንድትጠብቅ ለማሳሰብ በጸሎትና በብርቱ ተማጽኖ ጋር የቀረበ ጥሪ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል መሠረት

እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጐ በፈጠረው መሠረት በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል በሚሆን ጋብቻ ውስጥ ከሚደረግ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ውጪ የሚደረግ ማንኛውም የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ መሠረት ኃጢአት በመሆኑ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን የተወገዘ ነው (ዘፍ. 2:24፤ ዜሌ 20፡ 13፤ ሮሜ 1፡ 26-27 1 ተሰ. 4:2-5፤ ገላ. 5:19፤ ኤፌ. 5:3፤ ቈላ. 3:5፤ 1 ቆሮ. 6:16-20)።

የሰዎች ተፈጥሮአዊ ጾታና ሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማያሻማ መልኩ ተገልጧል (ዘፍጥረት 1:27)። ስለዚህ የሰዎች የወንድና ሴት ተፈጥሮአዊ ጾታ የሚበየነው በማህበራዊ የኑሮ ምርጫ፣ ልማድና ባህል ሳይሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በደነገገው ዘላለማዊ ሃሳቡና በማይሻረው ቃሉ ነው።

በዘፍ 2:24 ላይ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ተብሎ እንደተጻፈው አስቀድሞም እግዚአብሔር ጋብቻን በመለኮታዊ አሠራሩ ሲመሰርት በአንድ ወንድና አንዲት ሴት መሃከል የዕድሜ ልክ መጣመር እንደሚሆን ፈቃዱ ነው። ይህም አንድነት የማህበራዊ ጉዳይ ወይንም የሁለት ተጋቢዎች የጋብቻ ውል/ኮንትራት መፈራረም ብቻ ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን መለኮታዊና አንድ ሥጋ የመሆን ምስጢርም ነው። ጌታ ኢየሱስም በማቴ 19:4-6 ባለው ክፍል፤ “እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ። ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው። በማለት በዘፍጥረት የተነገረውን የጋብቻን መሠረት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ ጋብቻ ቅዱስ ሥርዓትና የማይፈርስ አንድነት መሆኑን በአጽንኦት የገለጸበት ሥፍራ ነው። በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር ቃል “ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው። አለም ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል” ሲል ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መሃከል የሚደረግ የተቀደሰ የእግዚአብሔር ተቋም መሆኑን በማያሻማ መልኩ ገልጿል።

ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን መለኮታዊ ሐሳብ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መሃከል ባለው ሕብረት ያመሳስለዋል። “ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ” ይላል (ኤፌ 5:31-33)። ሐዋሪያው የተጋቢዎችን የቃልኪዳን አንድነትና ፍቅር በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መሃከል ባለው ሕብረት አምሳያነት መግለጹ ጋብቻ መለኮታዊ ፍቅርና ተዓማኒነትን ያማከለ ምስጢር መሆኑን ከማመልከቱ በተጨማሪ እግዚአብሔር እንደፈጠረው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መሃከል የሚደረግ ቅዱስ ተቋም መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተመሳሳይም ቅዱሳት መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ቃልና የዘላለም ሐሳብ ውጭ የሚደረጉትን የሰዎችን ውድቀትና ብልሹ ባሕርያት በአጽንዖት ይኮንናሉ። ቅዱሳት መጻሕፍት የግብረሰዶማውያንን ባሕርያት በግልጽ በመቃወምና በማውገዝ ይህ ባህሪይ እግዚአብሔር ከደነገገው ከፍጥረት ሕግ ተቃራኒና የሰዎች የአመጽ ውጤት እንደሆነ ያስረዳሉ(ዘሌ 20፡ 13፤ ሮሜ 1፡ 26-27፤ 1ቆሮ 6፡ 9-11፤ 1ጢሞ 1፡ 10-11)። በ 1ኛ ቆሮ 6:9-10 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ከነዚህ ባህሪያት ተለዩ እያለ ከሚዘረዝራቸው ነገሮች ውስጥ አመንዝራነትና የተመሳሳይ ጾታ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ወይንም ወንድ ከወንድ ጋርና ሴት ከሴት ጋር የሚፈጽሙትን የግብረ ሰዶማዊነት ኃጢአት ይገኙበታል። ይህ ሁሉ አበክሮ የሚያስተምረው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ በነበረው ዓላማና መመሪያ መሠረት በቅድስናና በጽድቅ የሚኖርበት በአንድ ወንድና አንድ ሴት መሃከል የሚፈጸም በመልካም የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነምግባር የሚመራ ሥርዓት እንደሆነ ነው።

የሉተራን አስተምህሮም ጋብቻንና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በሚመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ መሠረታዊ ትምህርቶችን ያካትታል። ለግንዛቤ ያህልም ማህበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት በኦግስቡርግ ኮንፌሽን አንቀጽ 16 ላይ “አንድ ክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጸው በእግዚአብሔር የሞራል ሕግ እንዲኖር ይጠበቅበታል” ይላል። በተጨማሪም የክርስቲያን ሕይወት በበላይነት መመራት ያለበት ሕጸጽ-አልባ በሆነው በእግዚአብሔር ቃልና የሞራል ሕግ ሲሆን የሕብረተሰብ ሕግና ሥርዓት ከመለኮታዊው ሕግ በታች መታየት እንዳለበት ያስተምራል።

ከዚህም ሌላ አንቀጽ 24 (በሥርዓተ-ቅዳሴ ላይ / On the Mass) ስለ ቅዱስ ጋብቻ ሲናገር “ጋብቻ ክቡር ነው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መሃከል ያለውም ሕብረት የተቀደሰ ነው፤ አለማግባትንም ከጋብቻ አስበልጦ ማየት አግባብነት የለውም” ይላል። ይህንንም ሲል የሉተራን አስተምህሮ ጋብቻን ዝም ብሎ የተፈቀደ ጉዳይ እንደሆነ አርጎ ማሳየቱ ሳይሆን ለጋብቻ የታጩት ሁሉ ጋብቻ እግዚአብሔርን የሚያስከብር የተቀደሰ ሥርዓት መሆኑን እንዲረዱ ማስተማሩ ነው።

በተጨማሪም የኮንኮርድ ፎርሙላ ጽኑ በሆነው መግለጫው (Solid Declaration) ዶክትሪናችን በንጹህና በማያወላውል መልኩ መጠበቅ እንዳለበት ያስረግጣል። አንቀጽ ፲፩ “ማንኛቸውም አከራካሪ የመሠረተ ዕምነት ጥያቄዎች የሚፈቱት በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው” ይላል። ከዚህ መሠረታዊ መርሆ ውጭ ከጊዜው ጋር ተመሳስሎ እንሂድ በሚል ሰበብ የሚደረገው አካሄድ ከዕምነታችን መስመር ያስለቅቀናል። ደግሞም አማኞችን ስቶ ማሳት ይሆናል። ይህ ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ጢሞ 4:3-4 ጢሞቴዎስን ከመከረበትና ካስጠነቀቀበት ጋር ይመሳሰላል፤ “ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ” ይላል። እንደዚህ ዓይነቱ ማስጠንቀቂያ ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችውን የወንጌል አደራ ነቅታ በታማኝነት እንድትወጣውና ለእግዚአብሔር ቃል የማያወላውል አቋሟን ሳትሸራርፍ ይዛ እንድትዘልቅ ያሳስባል።

እነዚህንም መጽሐፍ ቅዱሳዊና የምንታመንባቸውን አስተምህሮዎች ስንመለከት አስቀድሞ እግዚአብሔር በቃሉ የደነገገው መለኮታዊ የሰዎች ጸታና ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የእምነታችን አካል በመሆኑ ጨርሶ ልናሻሽለው አልተፈቀደልንም።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የደነገገው የጋብቻ ሥርዓት ቅዱስና በንጽሕናም መጠበቅ ያለበት መለኮታዊ ሥርዓት ነው። ይህንንም የተቀደሰ ዕውነት ተግተን ለመጠበቅ ታማኝ ባለአደራዎች ተደርገን የተጠራን እንደመሆናችን ይህንን ዕውነት ዘመን አመጣሽ በሆነ አስተሳሰብ ልዩ ትርጉም በመስጠት መለኮታዊውን መገለጥ ለማሻሻል የሚደረገውን እንቅስቃሴ አጥብቀን እንቃወማለን። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሉተራዊ አቋማችንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከሚሲዮናዊ አገልግሎቶች ወይንም አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች ወይንም ስምምነቶች በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተመሠረተ መሠረተ እምነታችን የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል እንላለን።

የቤተ ክርስቲያናችንን የፖሊሲ ውሳኔ ለማስቀየር የሚደረገውን ጥረት ስለማውገዝ

ከላይ በግልጽ እንደተዘረዘረው በእግዚአብሔር ቃልና በሉተራን አስተምህሮ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ፲፱ኛው አቢይ ጉባኤ ፖሊሲ ውሳኔ መሠረት ላይ በመቆም እኛ የሰሜን አሜሪካ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ሉተራን ሕብረት፣ የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ ከአሜሪካ ወንጌላዊት ሉተራን ቤተ ክርስቲያን (ELCA) እና ከስዊድን ቤተክርስቲያን (Church of Sweden) ጋር ግንኙነቷን ለማደስ የምታደርገው እንቅስቃሴ እጅግ አደገኛ ስለሆነ በጥብቅ እንቃወማለን።

የሰሜን አሜሪካ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ሉተራን ቤተ ክርስቲያን አመታዊ ኮንፍራንሳችን በተካሄደ በሳምንቱ፡ ጁላይ 28፣ 2024 በተከበረው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የሰባኛ ዓመት እዮቤልዩ ማስጀመርያ ክብረ-በዓል ላይ የአሜሪካ ወንጌላዊት ሉተራን ቤተ ክርስቲያን (ELCA) ጳጳስና እና የስዊዲን ቤተ ክርስቲያን (Church of Sweden) ጳጳስ በክብር እንግድነት መጋበዛቸውና ንግግር ማድረጋቸው የቤተ ክርስቲያናችንን ፲፱ኛ አቢይ ጉባኤ የፖሊሲ ውሳኔ የጣሰ አሳዛኝ ድርጊት ነው። ይህም ድርጊት በደስታ መከበር ባለበት በዓል ላይ ክፉ ጥላ ማጥላቱ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ድርጊት ነው። ይህ አደገኛ አካሄድ መሪዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጤናማ አስተምህሮና የቤተ ክርስቲያኒቱ የፖሊሲ ውሳኔ ርቀው ረጅም መንገድ እንደተጓዙ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አካሄድ ከእግዚአብሔር ሃሳብ ጋር የሚጋጭና የቤተ ክርስቲያኒቷን ጤናማ አስተምህሮና አንድነት የሚፈታተን ከምንገልጸው በላይ እጅግ የሚያሳዝን ድርጊት ስለሆነ በጽኑ እንቃወማለን።

እውነተኛ ሚሲዮናዊት ቤተክርስቲያን እንደ እግዚአብሄር ቃል ኃጢአተኛ ከክፉ መንገዱ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ጥሪ የምታደርግ የክርስቶስ የፅድቅ መንግስት ወኪል ስለሆነች የእግዚአብሔር ቃል ኃጢያት ያለውን ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው በማለት በንስሃ ለሚመለሱ በወንጌል የሚገኘውን የኃጢያት

ይቅርታ ታውጃለች። የኢ.ወ.ቤ.ክ.መ.ኢ የሚሲዮናዊነት ተልዕኮ በዚሁ አግባብ ከጌታ የተሰጣትን ተልዕኮ ትወጣለች እንጂ የቃሉ እውነትና ስልጣንን ባለመቀበል ከፀኑ ጋር ቅይጥና መሰረት የለቀቀ ተልዕኮ ሊኖራት አይገባም:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያኒቱ “የትድግና ተልዕኮ” በማለት አሁን የጀመረችው አካሄድ ከጤናማ ተልዕኮዋ ጋር የማይጣጣም እና ስህተት ስለሆነ በአስቸኳይ እንድትታቀብ የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ይህ ጽኑ አቋማችን የቤተ ክርስቲያን ወግ ጠባቂዎች የመሆን ጉዳይ ሳይሆን ዘመን የማይቀይረው የእግዚአብሔር ቃል በማንኛውም ጉዳይ ላይ የበላይ መመሪያችን መሆኑንና፤ ለሉተራን አስተምሮአችንም ታማኞች መሆን እንዳለብን አበክረን የምንገልጽበት አቋም ነው። ማንኛውም “የትድግና ተልዕኮ” (rescue mission) በሚል ሰበብ ስነ-ጸታንና ጋብቻን በሚመለከት ቃሉንና የሉተራንን አስተምህሮ ከጣሱት ጋር የሚደረግ ግንኙነት መሠረተ እምነታችንን እንደ መሸቀጥና የተጠራንለትን የክርስቶስን እውነት ምስክርነት እንደ ማቃለል እናየዋለን።

የታማኝ ባሪያ ጥሪ

እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የወንጌላዊት መካነ የሱስ ሉተራን ሕብረት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ የሱስን መሪዎችንና ምዕመናንን ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ እንደተጻፈውና በሉተራን አስተምህሮዎች እንደተገለጸው በመሠረተ እምነታችን ላይ ጸንተው እንዲቆሙ አጥብቀን እናሳስባለን። ከአጋር ቤተ ክርስቲያናትና ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ትብብር የእግዚአብሔርን ቃል በመሸርሸር ሳይሆን መሠረታዊ ዕምነታችንን በጋራ ለማክበር ቁርጠኝነትን በማሳየት ሊሆን እንደሚገባ እናምናለን። የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት ከሚያዳክምና ምዕመናን በዕምነታቸው እንዲጠራጠሩ ወይንም ከመስመር እንዲወጡ ከሚያደርግ ማንኛውም ተግባር በጥንቃቄ እራሳችንን መጠበቅ ግድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀዋል “ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ” (2ኛጢሞ 4:3-4)። ከአሁኑ ዘመን ባሕልና ልምምዶች ጋር መመሳሰል እንደሥልጣኔ ተደርጎ በሚታይበት በዚህ የታሪክ ወቅት ላይ ይህ ማስጠንቀቂያ ምን ያህል ዕውነተኝነትና የዘመኑ መልዕክት እንደሆነ ማስተዋል አያዳግትም። ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቱን የሕብረተሰብ፤ የፖለቲካና፤ የአጋሮች ጫና መቋቋምና ባመነችበት የእውነት መሠረት ላይ ጸንታ መቆምና መቃወም ይጠበቅባታል።

ይህ አቋማችን በምዕራቡ ዓለም ያለችው ቤተ ክርስቲያን እንዴት ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር ቃል እየተንሸራተተች በስህተት ትምህርት እንደ ወደቀች ግንዛቤ ከማግኘት የመጣ ሲሆን፣ ለምዕመናን ሁሉ መንፈሳዊ ደህንነት ከማሰብ የመነጨ የማንቂያ ደወልና ብርቱ የሆነ የፍቅር ጥሪ እንደሆነ እንዲታወቅልን እንሻለን። በክርስቶስ አካል ውስጥ እውነተኛ አንድነት በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ላይ በመመሥረት የሳቱትን ወደ ንሥሐ መጥራት፤ እራሳችንን ከቃሉ ጋር ማገናዘብና፤ ያለማወላወል ትዛዛቱን ለመጠበቅ ጽኑ አቋም ማሳየት ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስንና ምዕመናኖቿን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃልና በሉተራን አስተምህሮ ላይ የተመሠረተውን ዕምነታችንን ጸንተን እንጠብቅ እንላለን። በተመሳሳይም ማንኛውንም ከዚህ መሠረት ፈቀቅ የሚያደርገውን፤ ዕምነታችንን የሚበርዘውንና፤ ምስክርነታችንን የሚያዳክመውን ከመሠረተ እምነታችን የመንሸራተት አካሄድ ጸንተን እንቃወማለን።

በክርስቶስ ለሆኑት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንዲሁም ለአሜሪካ ወንጌላዊት ሉተራን ቤተ ክርስቲያንና (ELCA) ስዊድን ቤተ ክርስቲያን (Church of Sweden) ጭምር ትልቅ ፍቅርና አክብሮት እንዳለን ይህም የአቋም መግለጫ የወጣው በዚሁ መንፈስ እንደሆነ እንዲታወቅልን እንወዳለን። በእግዚአብሔር ቃል እንደተጻፈው ዕውነተኛ ፍቅር ዕውነትን በፍቅር እንድንገልጥ ያስገድደናል። የእግዚአብሔር ቃል “ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ” ይላል (ኤፌ

4:15)። ይህ አቋም ከጊዜው ጋር የማይሄድና ኋላ ቀር የሚያሰኝ ቢሆንም የሳቱት ንስሐ እንዲገቡ አስተምህሯቸውም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንዲታረቅ ማሳሰብ እንደቃሉ ነው፤ እውነተኛ መንፈሳዊነትም ነው ብለን እናምናለን። እውነተኛ ሚሲዮናዊት ቤተክርስቲያን ኃጢአተኛን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር የምትመልስ፤ የክርስቶስንም ሞት ዋጋ የማታሳንስ፤ ሕግና ወንጌልን ያማከለ አገልግሎት የምትሰጥ ናት።

ምንም እንኳን ከጊዜው ጋር እንድንመሳሰል ጫናው ከባድ ቢሆንም የተጠራነው ዘመኑን እንድንለይና/እንድንዋጅ (ማቴ 16:3 ና ኤፌ 5:16) እንዲህ ዓይነቱን ጊዜ እንድንቋቋመው መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ሮሜ 12:2 እንዲህ ይመክረናል፤ “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” በዚህም መንፈስ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ዘመናት በማይሽሩትና በማይቀይሩት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጸንታ እንድትቆም፣ ይህንንም እምነቷን እንድታመቻምችና ከቃሉ እውነት ፈቀቅ እንድትል የሚደረገውን ጫና እንድትቋቋም አጥብቀን እንማልዳለን፣ እየጸለይንላትም እንገኛለን።

የዶ/ር ማርቲን ሉተር በከባድ ተቃውሞና በስደት ፊት ለፊት ያለማወላወል ለእውነት መቆም እኛንም ለተጠራንበት ጥሪ በታማኝነት እንድንቆም አስተምሮናል። እኛም እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ በቃሉ ላይ ታምነን ያለማወላወል ልንቆም ግድ ይለናል። ይህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተመሠረተው የሰው ልጅ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሥነ ምግባር አስተምህሮ ላይ ለመቆም ቁርጠኛ አቋም መውሰዳችን በግልጽ የተቀመጠውን የእግዚአብሔርን ቃል እንደገና ለመከለስና ለመበረዝ ለምትዳዳው ዓለማችን ብርሃንና ተስፋ ሰጭ እንዲሆን ጸሎታችን ነው። በዘፍጥረት እንደተተረከውና በቅዱሳት መጻሕፍት በተደጋጋሚ የተጻፈው መለኮታዊው የሰው ልጅ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሥነ ምግባር የግለሰቦች ወይንም ጊዜ አመጣሽ ባህላዊ ምርጫ ሳይሆን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መገለጥ፤ ጥበብና፤ ፍቅሩ ነው እንላለን።

ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያናችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያፈነገጡ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንድትፈጥር ከተፈለገ በዚህ ጉዳይ ያለው ብቸኛ አማራጭ ከእውነት ያፈነገጡ ግለሰቦችም ሆነ አብያተ ክርስቲያናት ንስሐ መግባትና ወደ እውነት መመለስ ብቻ ነው። እያወቁ እውነትን ከሚያጣምሙ ሰዎች መለየት እንደሚያስፈልግ የእግዚአብሔር ቃል አጥብቆ ያስተምራል (ሐዋ. 20፡29-31፤ 1ቆሮ. 5፡1-11፤ 2ቆሮ. 2፡17፤ ማቴ. 18: 15-20)። ቤተ ክርስቲያናችን የክርስቶስ አካል በመሆኗ ይህንን ድርጊት በቤተ ክርስቲያን ተግሣጽ ተግባር ድንጋጌ መሠረት መፈጸም አለባት።

በመጨረሻም የአቋም መግለጫችንን የምንቋጨው የዶ/ር ማርቲን ሉተርን ቃል፣ “አቋሜ ይኸው ነው! ከዚህ ውጭ የማደርገው የለም፤ አምላኬ ሆይ እርዳኝ” በማለት ነው።

ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ሉተራን ሕብረት በሰሜን አሜሪካ
Mekane Yesus Lutheran Fellowship in North America
Chicago, July 20, 2024